# የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## ለውጭ አገር ዜጎች
## የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን
## ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

ጥር 2002 ዓ.ም.
አዲስ አበባ



www.chilot.me

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

# የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

### 1. አውጭው ባለሥልጣን

"የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 170(1)(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. አውጥቶ በሥራ ላይ ያለውን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህንን የማሻሻያ መመሪያ አውጥቷል፡፡"

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "አሠሪ" ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2(1) ያለው ትርጉም ይኖረዋል፡፡
2. "ሚኒስቴር" ማለት የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡
3. "ተገቢው ሙያ" ማለት የውጭ አገር ዜጋው ለሚቀጠርበት የሥራ መደብ ብቃት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ የትምህርት ማስረጃ ወይም የክህሎት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ወይም የሥራ ልምድ ነው፡፡
4. "ተተኪ ሠራተኛ" ማለት የውጭ አገር ዜጋው በተመደበበት የሥራ መደብ ላይ በረዳትነት ተመድቦ የውጭ አገር ዜጋውን ለመተካት ዕውቀት የሚቀሰም ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ ማለት ነው፡፡
5. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴትም ያገለግላል፡፡



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

6. “የሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት” ማለት እንደጉዳዩ ሁኔታ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ለመሥራት የሥራ ፈቃድ እንዲወጣላቸው ጥያቄ ለሚቀርብላቸው የውጭ አገር ዜጎች የድጋፍ ደብዳቤ ወይም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥ አካል ነው፡፡

## 4. የሥራ ፈቃድ ስለማውጣት

1. ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በማናቸውም የሥራ መስክ ተቀጥሮ ለመሥራት የሚችለው ከሚኒስቴሩ ወይም ሕጋዊ ውክልና ከተሰጠው የፌዴራል ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተሰጠ ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ ሲይዝ ብቻ ነው፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን በድርጅቱ ውስጥ ለመቅጠር ሲጠይቅ ብቻ ነው፣

3. የሥራ ፈቃድ የሚያገለግለው ፈቃዱን በጠየቀው አሠሪ ድርጅት ውስጥ ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መደብ ላይ ለመሥራት ብቻ ነው፡፡

## 5. የሥራ ፈቃድ ማውጣት የማያስፈልጋቸው የውጭ አገር ዜጎች

ከዚህ በታች የተመለከቱት የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አያስፈልጋቸውም፡፡

1. የኢትዮጵያ ተወላጅ ሆነው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዙ የውጭ ዜጎች፣

2. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚያረጋግጠው መሠረት፡-

ሀ/ የዲፕሎማቲክ ሚሽን አባሎች፣
ለ/ የቆንስላ አባሎች፣
ሐ/ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች፣
መ/ የአፍሪካ ሕብረት አባሎች፣
ረ/ የዓለም ባንክ አባሎች፣
ሰ/ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባሎች፣
ሸ/ የዓለም አቀፍ አቶሚክ ኃይል ወኪል አባሎች እና
ቀ/ ሌሎች ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ድርጅቶች፣


Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው የውጭ አገር ዜጋ በተለየ ሁኔታ የሚቀጠር ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት የሥራ ፈቃድ ሊወጣለት ይገባል፡፡

## 6. የሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎች

ማናቸውም አሠሪ በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋን ቀጥሮ ለማሰራት የሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚችለው፣

1. የውጭ አገር ዜጋው ለሥራው ተገቢው ሙያ ያለውና አስፈላጊ መሆኑን በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ፣

2. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 9 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ አገር ዜጋው የመንግስት ባልሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ በዕርዳታ መልክ የትምህርት የጤናና ይህን የመሳሰሉ የማኅበራዊ አገልግሎት ለመሥጠት የተሰማራ ሆኖ አገልግሎቱም ለሀገሪቱ ጠቃሚና ተፈላጊነት ሲኖረው፣

3. ዋና መሥሪያ ቤቱ ከኢትዮጵያ ውጭ የሆነው ድርጅት ወክሎ ተቀማጭነቱን በኢትዮጵያ ውስጥ አድርጎ የሚሠራ የውጭ አገር ዜጋ ሥራው ለኢትዮጵያውያን የሥራ መስክ የሚከፍትና የመቀጠር ዕድልን የማይዘጋ ሲሆን፣

4. የውጭ አገር ዜጋው በከፊል የባለቤትነት መብት በሆነ ድርጅት ውስጥ በደመወዝ ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን፣ እንዲሁም፡-

5. የውጭ አገር ዜጋው መንግሥት ባደረገው የሁለትዮሽ ወይም የብዙ ወገን ስምምነቶች ወይም ውሎች መሠረት ሲቀጠር፣

6. አሠሪው/የውጭ ባለሀብት ብቻውንም ሆነ ከአገር ውስጥ አሠሪ/ባለሀብት ጋር በቅንጅት ላቋቋመው ድርጅት ከፍተኛ የማኔጅመነት አባላት የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን ለመቅጠር ሲፈለግና ቅጥሩም ሥራ ላልጀመረ ድርጅት በኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ሥራ ከጀመረ ደግሞ በሚኒስቴሩ መ/ቤት ሲረጋገጥ፣



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

7. አሠሪው/የአገር ውስጥ ባለሀብት ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ ከውጭ ኢንተርፕራይዝ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት የውጭ አገር ዜጋው ለሥራው አስፈላጊ መሆኑን በኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ሲረጋገጥ የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

## 7. <u>ስለ ሥራ ፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም አሠሪ የውጭ አገር ዜጋ ለመቅጠር የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ለማቅረብ የሚችለው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገው የማመልከቻ ቅጽ የሚጠይቀውን መረጃ በማሟላት ነው፣

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(2)(3)(4) እና 6(6) እንዲሁም ቀጣይነት በሌላቸው እንደ መሣሪያ ተከላ፣ ሱፐርቪዥን፣ የኦዲትና የሂሳብ ሥራ ላይ ከሚቀጠሩት በስተቀር በሌሎች የሥራ መደቦች ለሚቀጠር የውጭ አገር ዜጋ ተተኪ ኢትዮጵያዊ መመደቡን ወይም መቀጠሩን የሚገልጽ ማስረጃ በአሠሪው ይቀርባል።

3. አሠሪው ለተተኪ ኢትዮጵያውያን ስለሚሰጠው የዕውቀት ሽግግር ፕሮግራምና ስለሚተኩበት የጊዜ ገደብ መግለጫ ያቀርባል።

4. አሠሪው በጤናና በትምህርት ዘርፍ የሚቀጠሩ የውጭ አገር ዜጎችን በተመለከተ እንደአግባቡ ከሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያቀርባል።

5. ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች ማስረጃዎችን ወይም መግለጫዎችን አሠሪው እንዲያቀርብ መጠየቅ ይችላል።

## 8. <u>ተተኪ ኢትዮጵያውያንን ስለማሰልጠን</u>

1. አሠሪው የሥራ ፈቃድ በተሰጠበት የጊዜ ገደብ ውስጥ የውጭ አገር ዜጎችን የሚተኩ ኢትዮጵያውያን እንዲሰለጥኑ በማድረግ ወቅታዊ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

2. ስለተተኪው ኢትዮጵያዊው አጠቃላይ የዕውቀት ሽግግርና የሥራ ሁኔታ በሚኒስቴሩ በኩል ክትትል ይደረጋል።



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

## 9. ከሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ስለሚሰጥ ማረጋገጫ

አሠሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(2) መሠረት የሥራ ፈቃድ የሚጠየቅለት የውጭ አገር ዜጋ ስለሚሰራው ሥራ ወይም ስለሚሰጠው አገልግሎት ጠቃሚነት አግባብ ካለው የመንግሥት መ/ቤት የተሰጠ የጽሑፍ ማረጋገጫ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡

## 10. የሥራ ፈቃድ የጊዜ ወሰንና ዕድሳት

1. የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው በአንድ የሥራ መደብ ለማገልገል እስከ ሦስት ዓመት ሲሆን፣ በየዓመቱ ይታደሳል፡፡ ሆኖም ሚኒስቴሩ የሦስት ዓመቱን የጊዜ ገደብ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

2. የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ የቀረበበት ምክንያት በቂ ሆኖ ካልተገኘ ሚኒስቴሩ የሥራ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፣

3. የሥራ ፈቃድ የሚራዘመው በአንድ ጊዜ ከሦስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሲሆን በየዓመቱ ይታደሳል፣

## 11. የአሠሪ ግዴታዎች ፣

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ያሉት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አሠሪው የሚከተሉት ተጨማሪ ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

1. ተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጋው ከሥራ ቦታ ከተሰወረ አሠሪው ሠራተኛው መጥፋቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ2 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2. የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው የውጭ አገር ዜጋው በአካል እንዲቀርብለት ሲጠይቅ አሠሪው አስፈላጊውን የመፈፀም ግዴታ አለበት፣

3. አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን አገልግሎት የማይፈልግ ሆኖ የሥራ ውሉን ሲያቋርጥ የሥራ ውሉን ባቋረጠ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለሚኒስቴሩ አሳውቆ የሥራ ፈቃድ ደብተሩን መመለስ አለበት፡፡



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

4. የውጭ አገር ዜጋው የሚሠራበትን የሥራ ቦታ ከቀየረ አሠሪው አዲሱን አድራሻ፣አድራሻው ከተቀየረበት ቀን ጀምሮ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

5. ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የአገሪቱን ሕጎች መጣሱ ሲረጋገጥ አሠሪው ወዲያውኑ የሥራ ፈቃዱን ለሚኒስቴሩ አቅርቦ እንዲሰረዝ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

6. አሠሪው የሥራ ፈቃድ የሌለውን የውጭ አገር ዜጋ በሥራ ላይ ማሰማራት የለበትም፡፡

7. አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን የመኖሪያ አድራሻ መዝግቦ በመያዝ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የማሳየት/ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

8. አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን በሕገወጥ ሥራዎችና በሌላ ለሞራል ተጻራሪ በሆኑ ተግባራት ላይ ማሰራት የለበትም፡፡

## 12. <u>የተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ ግዴታዎች</u>

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ያሉት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

1. ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ በሥራ ፈቃድ ደብተሩ ላይ ከተመለከተው አሠሪ ውጪ ለሌላ አሠሪ መሥራት የለበትም፣
2. የውጭ አገር ዜጋው የሥራ ፈቃድ ካልያዘ በሥራ ላይ መሠማራት የለበትም፡፡
3. ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ መሥራት የሚችለው በሥራ ፈቃድ ደብተሩ ላይ በተመዘገበው የሥራ መደብ /ሙያ ብቻ ነው፡፡
4. ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ በሕገወጥ ሥራዎችና በሌላ ለሞራል ተፃራሪ በሆኑ ተግባራት/ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ቢገኝ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
5. የውጭ አገር ዜጋው ወደ ሚኒስቴሩ በመቅረብ ሪፖርት እንዲያደርግ በሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው ሲጠየቅ በወቅቱ የመቅረብ ግዴታ አለበት፡፡



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

## 13. አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፣

1. ማንኛውም አሠሪ ለሚቀጥረው የውጭ ዜጋ አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

   ሀ. የሥራ ፈቃድ ጥያቄ የተሞላበትን ቅጽ፣

   ለ. የውጭ አገር ዜጋውን የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

   ሐ. የውጭ አገር ዜጋውን የጉዞ ሰነድ ኮፒ፣

   መ. የተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የግል ታሪክ የተሞላበትን ቅጽ፣

   ሠ. የፓስፖርት መጠን ያላቸው የውጭ አገር ዜጋው አራት ጉርድ ፎቶግራፎች፣

   ረ. ጊዜው ያላለፈበት የቢዝነስ ቪዛ፣

2. አሠሪው መንግስታዊ ድርጅት ከሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 13/1/ ከተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

   ሀ. ፕሮጀክቱን/ሥራውን በቀጥታ ከሚቆጣጠረው የመንግሥት ድርጅት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

   ለ. የውጭ አገር ዜጋው በጤና ወይም በትምህርት ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሠማራ ከሆነ እንደአግባቡ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

3. አሠሪው የግል ድርጅት ከሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 13 /1/ ከተመለከቱት በተጨማሪ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፣

   ሀ. እንደአግባቡ የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

   ለ. እንደአስፈላጊነቱ አግባብ ካላቸው አካላት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

4. አሠሪው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 13/1/ ከተመለከቱት በተጨማሪ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ሀ/ በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ

ለ/ የውጭ አገር ዜጋው በጤናና በትምህርት ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሰማራ ከሆነ እንደ አግባቡ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

ሐ/ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ምዝገባ ኤጀንሲ የተሰጠ የምዝገባ ሰርተፊኬት፣

መ/ ተቀጣሪው በማኅበራት ውስጥ በሥራ የሚሠማራ ከሆነ አግባብ ካለው ድርጅት/መ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ፣

## 14. ለሥራ ፈቃድ ዕድሳት የሚጠየቁ መስፈርቶች ፣

1. የውጭ አገር ዜጋውን የሥራ ፈቃድ ለማደስ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

   ሀ/ የውጭ አገር ዜጋው የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ማመልከቻ፣

   ለ/ የውጭ አገር ዜጋው ፓስፖርትና ሌሎች የጉዞ ሰነዶች፣

   ሐ/ ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ደብተር፣

   መ/ የመኖሪያ ፈቃድ፣

   ሠ/ የተተኪ ኢትዮጵያውያንን የዕውቀት ሽግግር በተመለከተ ሪፖርት፣

2. አሠሪው የመንግሥት ድርጅት ከሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 14/1/ ከተመለከቱት በተጨማሪ የውጭ አገር ዜጋው በጤና ወይም በትምህርት ዘርፍ ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ እንደአግባቡ ከጤና ጥበቃ ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

3. አሠሪው የግል ድርጅት ከሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 14/1/ ከተመለከቱት በተጨማሪ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

   ሀ/ የታደሰ የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

   ለ/ እንደአግባቡ ከሚመለከታቸው አካላት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ሐ/ የውጭ አገር ዜጋው በጤናና በትምህርት ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሠማራ ከሆነ እንደአግባቡ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

4. አሠሪው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 14/1/ ከተመለከቱት በተጨማሪ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ/ በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

ለ/ የውጭ አገር ዜጋው በጤና ወይም በትምህርት ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሠማራ ከሆነ እንደአግባቡ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

ሐ/ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ የተሰጠ የምዝገባ ሠርተፊኬት፣

መ / የውጭ አገር ዜጋው በማኅበራት ውስጥ በሥራ የሚሠማራ ከሆነ የድጋፍ ደብዳቤ አግባብ ካለው ድርጅት የድጋፍ ደብዳቤ፣

## 15. <u>የሥራ ፈቃድን ስለማራዘም</u>

1. በዚህ መመሪያ በሌላ አኳኋን የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ፈቃድ ሊራዘም የሚችለው፡-

   ሀ/ ተተኪው ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋውን የሥራ መደብ መሸፈን ሳይችል ሲቀር ወይም

   ለ/ የውጭ አገር ዜጋው ለሥራው አስፈላጊ ሲሆን እና የተቀጠረበትም ሥራ ቀጣይና አስፈላጊ መሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ የሥራ ፈቃዱ ሊራዘምለት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም አሠሪው/የውጭ ባለሀብት ብቻውንም ሆነ በቅንጅት ለሚያቋቁመው ድርጅት በከፍተኛ የማናጅሜንት ቦታ ለቀጠረው የውጭ አገር ዜጋ የሥራ ፈቃድ እንዲታደስለት እንዲሁም እንዲራዘም ሲጠይቅ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

## 16. የሥራ ፈቃድን ደብተር ስለመተካት

1. የሥራ ፈቃድ ደብተር ሲጠፋ አሰሪው ደብተሩ መጥፋቱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ደብተሩ የጠፋበትን ምክንያት የሚገልጽ ድርጅቱን የሚወክል አግባብ ባለው ሰው የተፈረመ መግለጫ ለሚንስቴሩ ማቅረብ አለበት፣
2. አሠሪው በንዑስ ቁጥር 1 ከተገለጸው በተጨማሪ የሥራ ፈቃድ ደብተር ለመጥፋቱ የፖሊስ ማስረጃ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ የቀረበውን ማስረጃ በማረጋገጥ ምትክ የሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል፣

## 17. የሥራ ፈቃድ ክሊራንስ

ማንኛውም አሠሪ የሥራ ፈቃድ ላወጣለት የውጭ አገር ዜጋ ክሊራንስ ሲፈልግ የሚከተሉትን አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ከቀጣሪው ድርጅት የሚቀርብ የክሊራንስ ጥያቄ ማመልከቻ፣

ለ/ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ አገር ዜጋው የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ደብተር፣

## 18. የሥራ ፈቃድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

1. የሥራ ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ይሠረዛል፡-

ሀ/ የውጭ አገር ዜጋው የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ከጨረሰ በኋላ ለሥራው አስፈላጊ አለመሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ፣

ለ/ የውጭ አገር ዜጋው የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ የጊዜ ወሰን ባይጨርስም ለሥራው አስፈላጊ አለመሆኑ በአሠሪው ወይም በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የውጭ አገር ዜጋው ፈቃድ በተጠየቀለት ሥራ ላይ ሳይሆን በሌላ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሲገኝ፣

መ/ የውጭ አገር ዜጋው ሲሰራው የነበረው ሥራ ሲያልቅ ወይም የማያስፈልግ ሲሆን ወይም ድርጅቱ ሲዘጋ፣

ሠ/ የሥራ ፈቃዱ አለበቂ ምክንያት በወቅቱ ሳይታደስ ሲቀር፣

ረ/ የውጭ አገር ዜጋው በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ለአገሪቱ ደህንነት አስጊ መሆኑ አግባብ ባላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ሲረጋገጥ ወይም

ሰ/ የውጭ አገር ዜጋው ሥራውን ሲለቅ እና



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional
www.chilot.me

ሸ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና 12 የተጠቀሱት የአሠሪና የሠራተኛ ግዴታዎች ሳይፈጸሙ ሲቀሩ ነው፡፡

2. የሥራ ፈቃድ ሲሰረዝ አሠሪው የሥራ ፈቃድ ደብተሩን ለሚኒስቴሩ መመለስ አለበት፣

## 19. ቅጣት

1. በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ስለቅጣት የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ መሠረት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው የሚሰራ የውጭ አገር ዜጋ አግባብ ባለው አካል ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋል፡፡
2. ያለሥራ ፈቃድ የውጭ አገር ዜጋን ሲያሠራ የተገኘ አሠሪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ስለቅጣት የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡

## 20. ስለ አገልግሎት ክፍያ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በወሰነው መሠረት ፡-

1. አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት ብር 600.00 (ስድስት መቶ ብር)
2. የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ለማውጣት ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር)
3. የሥራ ፈቃድ ደብተር ለመተካት ብር 400.00 (አራት መቶ ብር) የአገልግሎት ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 21. የመተግበር ግዴታ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በተደነገጉትን ጉዳዮች የሚመለከተው አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 22. የተሻረ መመሪያ

ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን እንደገና ተሻሽሎ መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. የወጣው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

## 23. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተሰጠ የሥራ ፈቃድ በዚህ መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 24. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ______________________________ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ______________________________ ዓ.ም.

ሐሰን አብደላ

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional